# የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የ1995 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ
# ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1989 በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ የሂሣብ መረጃዎችን የበጀቱ ዓመት እንደተጠናቀቀ በተቻለ ፍጥነት ዘግቶ ለኦዲት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር እንደሚልክና ዋናው ኦዲተር መ/ቤትም የሂሣብ መግለጫው በደረሰው በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ኦዲት አድርጎ ሪፖርቱን ከነአስተያየቱ ለሚኒስቴሩ መላክ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የኢትዮጵያ የመንግሥት ሂሳብ የኦዲት ደረጃዎችን (Ethiopian Government Audit Standards) ተከትለን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የፌዴራል መንግሥት የ1995 በጀት ዓመት የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ፣ የሂሣብ መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች የሂሣብ መግለጫዎች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ዝርዝር የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ህጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን በመከተል መፈፀማቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

በአዋጅ ቁጥር 68/1989 መሠረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጁት የመንግሥት ሂሣብ መግለጫዎች የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው መዘጋጀታቸውን በኦዲት በማረጋገጥ ነፃ አስተያየት መስጠትና ሪፖርት ማቅረብ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ ሂሣቦች ላይ የተከናወነ ሲሆን የተሟላና ተገቢ ማስረጃ መኖሩን፣ የፋይናንስ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተከብረውና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶች ተጠብቀው ዝርዝር የሂሣብ እንቅስቃሴዎች መፈፀማቸውን እና የሂሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ያካተተ ነው፡፡

የቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ እንዲያስችለን ጉልህ የሆኑ ስህተቶች አለመፈፀማቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ የተሟላ ማስረጃና ማብራሪያ ለማግኘት በሚያግዝ ደረጃ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

አስተያየታችንን ለመስጠት እንዲያስችለን በሂሣብ መግለጫው የቀረበው የበጀት ዓመቱ የገቢና የወጪ ሂሣብ፣ እንዲሁም የሂሣብ ማስረጃ ጥንቅር አመዘጋገብ ሲታይ፣

1. ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተላለፈው የድጋፍና ልዩ ድጎማ በጀት ብር 4,897.4 ሚሊዮን የሂሳብ ሪፖርት ሳይቀርብ በቀጥታ ሥራ ላይ እንደዋለ ተደርጎ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

   የቀረበውም ዓመታዊ የገቢና ወጪ ሂሣብ ሪፖርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 መሠረት የክልል መንግሥታት የከተማ መስተዳድሮች የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ በሚያሳይ መልኩ አልተዘጋጀም፡፡

2. በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብ እና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/84 ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1987 አስቀድሞ ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ እና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም ከማሻሻያ አዋጅ ጀምሮ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት የዘቀጠ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

   ይሁን እንጂ በነዚህ አዋጆች መሠረት ከእያንዳንዱ ድርጅት ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ተሞክሮ የውዝፍ ዕዳ መከታተያ መዝገብ ከማስረጃዎች ጋር ለማገናዘብ በሚያስችል መልኩ ማጠቃቀሻ የሌለው በመሆኑ እና ማስረጃዎቹም በተሟላና ለኦዲት አመቺ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተው ለኦዲት ባለመቅረባቸው ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰቡን ማጣራት አልተቻለም፡፡

3. መንግሥት ከውጭ አገር ተበድሮ ለልማት ድርጅቶች ካበደረው ሂሳብ ውስጥ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ እስከ ሰኔ 30/1995 ዓ.ም ድረስ ያልተሰበሰበ ከአንድ አመት እስከ 10 ዓመታት በውዝፍነት የቆየ የዋና ገንዘብ (Principal) ብር 171 ሚሊዮን እንዲሁም የብድር ወለድ (Interest) ብር 464 ሚሊዮን በድምሩ 635 ሚሊዮን ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባደረጉት የብድር ስምምነት ላይ ከተጠቀሰው የብድር ገንዘብ መጠን SDR 127.4 ሚሊዮን በላይ በኮርፖሬሽኑ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል ተጨማሪ የብድር ስምምነት ሳይደረግ አበዳሪው እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባደረጉት የብድር ሽግሽግ ስምምነት መሠረት ለኮርፖሬሽኑ SDR 7,108,741.38 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ይህንንም ሁኔታ ለማስተካከል የውል ስምምነት የተዘጋጀና ከኮርፖሬሽኑ ጋር ለመፈራረም ዝግጅቱ መጠናቀቁን በኦዲት ወቅት ተገልጿል፡፡

4. በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው መንግሥት በ1995 በጀት ዓመት የተበደረውና የከፈለው የቀጥታ ብድር ከወጪ ቀሪ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫው ላይ ከተመለከተው በብር 466 ሚሊዮን አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሆነው የ1994 በጀት ዓመትን የችሮታ ክፍያ ለመሸፈን ሲባል ሂሳቡ በ1994 በጀት ዓመት በመመዝገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

5. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ መሠረት የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይታወጅ የተለያዩ ባለበጀት መ/ቤቶች በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች ብር 66.89 ሚሊዮን ከተደለደለው በጀት በላይ ተጠቅመው ተገኝተዋል፡፡ ከበጀት በላይ የተጠቀሙት መ/ቤቶች የተጠቀሙበትን ምክንያት የሚገልጽ ዘገባ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሂሳቡን በወጪ ከመመዝገብ በስተቀር ከበጀት በላይ በተጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡

6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቻናል 2 የተገኘን እርዳታ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ ለማካተት እያንዳንዱ መ/ቤት ያገኘውን እርዳታ እንዲያሳውቅ ደብዳቤ መፃፍ፣ የተለየ የእርዳታ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረግ እና መ/ቤቶች በእርዳታ ያገኙትን ገንዘብ ሥራ ላይ አውለው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ሪፖርት ሲያቀርቡ ሂሳቡን የመመዝገብ ተግባር እያከናወነ ቢሆንም፣ ባለበጀት መ/ቤቶች በቻናል 2 ያገኙትን እርዳታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁ ቢቀሩ ሪፖርት

ያላደረጉትን መ/ቤቶች ለማወቅና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ በቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የእርዳታ ገቢ ሂሳብ መንግሥት በበጀት ዓመቱ ያገኘው ዕርዳታ ይህ ብቻ ነው ብሎ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 በዝርዝር ከተገለፁት ልዩ ልዩ የአሰራር ግድፈቶች በስተቀር በእኛ አስተያየት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የዘመኑን የመንግሥት ሂሣብና የፋይናንስ አፈፃፀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ግኝቶች ዝርዝር ሁኔታዎችና የመፍትሄ ሀሳቦች በሪፖርቱ ከገጽ 5 ጀምሮ ተመልክቷል፡፡

## ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
## የ1995 በጀት ዓመት የገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት
## ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቀረበው አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የበጀት ዓመቱ የገቢ ሂሣብ በበጀት ዓዋጁ መሠረት መሰብሰቡንና ሂሣቡም በሪፖርት በትክክል የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 1. በበጀት ስለተያዘውና ስለተሰበሰበው ገቢ፡–

- በፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የገቢ እቅድ በ1995 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ የታወጀውና በተጨማሪ በጀት የተያዘው ብር 19,433.6 ሚሊዮን ሲሆን የተሰበሰበው ብር 14,914.4 ሚሊዮን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ብር 4,519.3 ሚሊዮን በእቅዱ መሠረት ያልተሰበሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የገቢው ዓይነት | የተስተካከለ በጀት | የተሰበሰበ ገቢ | የተሰበሰበው ገቢ በመብለጥ/በማነስ/ |
|---|---|---|---|
| ከአገር ውስጥ ቀጥታ ታክስ | 2,340.7 | 1,662.7 | (677.9) |
| ቀጥታ ካልሆኑ ታክሶች | 1,534.8 | 1,449.5 | (85.3) |
| ከውጭ ንግድ ቀረጥንና ታክስ | 4,624.9 | 3,633.8 | (991.1) |
| ከፈቃድና ሌሎች ክፍያዎች | 215.7 | 190.2 | (25.5) |
| ከመንግሥት አገል. እና እቃዎች ሽያጭ | 312.0 | 284.5 | (27.5) |
| ከመንግሥት ኢንቨስትመንት ገቢ | 1,187.7 | 1,457.8 | 270.1 |
| ልዩ ልዩ | 972.1 | 620.9 | (351.2) |
| የመደበኛ ገቢ ድምር | 11,188.0 | 9,299.5 | (1,888.5) |
| የካፒታል ገቢ | 572.2 | 367.4 | (204.8) |
| የውጭ አገር እርዳታ | 3103.7 | 1,955.4 | (1,148.3) |
| የውጭ አገር ብድር | 4569.8 | 3,292.1 | (1,277.7) |
| ጠቅላላ ድምር | 19,433.6 | 14,914.4 | (4,519.1) |

ከላይ እንደተመለከተው ብር 4,519.3 ሚሊዮን ሊሰበሰብ ያልተቻለበት ምክንያት እንዲገለጽ ለኦዲት አስደራጊዎች ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም አጥጋቢ መልስ አልተሰጠም። ስለሆነም የበጀት ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት በበቂ ጥናትና በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን እንዲሁም የገቢ አሰባሰብ ሊጠናከር ይገባል።

- በበጀት ሳይያዝ በተለያዩ የገቢ አርዕስቶች ብር 383 ሚሊዮን ተሰብስቦ ተገኝቷል። በመሆኑም በበጀት ዝግጅት ወቅት ያለፉት አመታትን ገቢዎች ግምት ውስጥ በማስገባትና በቂ ጥናት በማድረግ ገቢ ሊሰበሰብባቸው የሚችሉ አርዕስቶች በበጀት እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል።
- በበጀት አዋጁ የታወጀው ገቢና በተጨማሪ በጀት የተያዘው ገቢ በገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫው በትክክል የተመለከተ መሆኑ ሲጣራ በገቢ አርዕስት 3210 ብር 40,000 በሂሳብ መግለጫው ሳይያዝ ተገኝቷል። በመሆኑም ሂሣብ በሚጠቃለልበት ወቅት ጥንቃቄ ተደርጎ መጠቃለል የሚገባቸው ሂሳቦች ሁሉ በመግለጫው ሊካተቱ ይገባል።

## 2. የኢንቨስትመንት ገቢ፡-

በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብ እና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ መክፈል ያለባቸው ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 25/84 ደግሞ የትርፍ ድርሻ ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ተደንግጓል። በዚህ አዋጅ ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1987 አስቀድሞ ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የዘቀጠ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል። በዚሁ መሠረት ከዘቀጠ ትርፍ ብር 521,000,000 የተሰበሰበ መሆኑ በቀረበው ዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ ላይ ለማወቅ ተችሏል።

ይሁን እንጂ ከአዋጅ ቁጥር 25/1984 በፊት የነበረው ውዝፍ የዋና ገንዘብና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 163/71 የሚተዳደሩት ድርጅቶች የሚፈለግባቸውን የዘቀጠ ትርፍ እና ከአዋጅ ቁጥር 121/1987 በፊት የሚፈለግባቸውን የዋና ገንዘብ መሰብሰቡን ለማጣራት ተሞክሮ በእያንዳንዱ

ድርጅት ስም በተያዘው ሌጀር ላይ በዴቢትና ክሬዲት የተመዘገቡትን ሂሳቦች ከማስረጃዎቻቸው ጋር ማነፃፀር የሚያስችል ማጠቃቀሻ የሌለው በመሆኑ፣ የተሟላና ለኦዲት ሥራ አመቺ ሆኖ ባለመገኘቱ እንደዚሁም በበጀት ዓመቱ ተሰብስቧል ተብሎ የቀረበው ሂሳብ በዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ ከተያዘው ጋር ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ኦዲቱን ለማከናወን አልተቻለም፡፡

ውዝፍ እዳቸውን በማይከፍሉ ድርጅቶች ላይ እየተደረገ ስላለው ክትትልና እርምጃ ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር በመሆን ያለባቸውን እዳ እንዲከፍሉ በተለያየ ጊዜያት ደብዳቤ የተፃፈላቸው ቢሆንም አንዳንዶቹ ለመክፈልም ሆነ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸውን፣ ሌሎቹ ደግሞ መክፈል የማይችሉ መሆኑን የገለፁ በመሆኑ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ማስታወሻ የቀረበ መሆኑ፣ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች ላይ ድርጅቶች ባይከፍሉ የሚገደዱበትን አንቀጽ በግልጽ ያላስቀመጠ ስለሆነ በአፈፃፀም ላይ ችግር ያስከተለ መሆኑን፣ ይህን ገንዘብ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እንዲሰበስብ ቢደረግ የተሻለ አፈፃፀም ሊኖር ይችል እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ስለሆነም የውዝፍ እዳ መከታተያ መዝገብ በተሟላ ማስረጃ የተደገፈ በማድረግ ምዝገባው በወቅቱ ሊከናወን ይገባል፡፡ አዋጆቹን ለማስፈጸም የአስገዳጅነት ሁኔታ ይጐድለዋል ከተባለ ጉዳዩን ለመንግሥት አቅርቦት የሚሻሻልበትን መንገድ በመፈለግ፣ ዕዳቸውን በማይከፍሉ ድርጅቶች ላይም ጠበቅ ያለ እርምጃ በመውሰድ እንዲከፍሉ ማድረግ፣ ሊከፈል የማይቻልበት ሁኔታ ካለ ትኩረት ተሰጥቶት በመንግሥት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

3. <u>**የመልሶ ማበደር ሂሣብ**</u> :-

መንግሥት ከውጭ አገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነቶች ለልማት ድርጅቶች መልሶ ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሰረት ወቅቱን ጠብቀው መክፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከ30 ብድሮች ሊሰበሰብ የሚገባው የብድር ተመላሽ ሂሳብ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከልማት ድርጅቶች የሚፈለገው ተሰብሳቢ ሂሳብ በውል ስምምነቱ መሠረት ተገቢው ክትትል ተደርጎ ተመላሽ እንዲሆን ያልተደረበትን ምክንያት ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው፣

- በ36 ብድሮች ብር 29.8 ሚሊዮን ዕዳ ያለባቸው 5 ድርጅቶች በመንግሥትና በባለአክሲዮኖች ውሳኔ እንዲሁም በኪሳራ የፈረሱ መሆኑ፣
- በ7 ብድሮች ብር 132.7 ሚሊዮን ዕዳ ያለባቸው 4 ድርጅቶች ፈርሰው ዕዳቸው ወደ ሁለት ባለበጀት መ/ቤቶች የተላለፈ መሆኑ፣
- በ6 ብድሮች ብር 205.9 ሚሊዮን ዕዳ ያለባቸው 4 ድርጅቶች ወደ አክስዮን ማህበርነት የተቀየሩ ሲሆን፣ እነዚህን ድርጅቶች ወደ ግል ለማዞር በሂደት ላይ በመሆናቸውና በቀጣይም ዕዳው ወደ መንግሥት የሚተላለፍ መሆኑ፣
- በ3 ብድሮች ብር 15.6 ሚሊዮን ዕዳ ከነበረባቸው 2 ድርጅቶች ጋር የነበረው የብድር ስምምነት ተቋርጦ ገንዘቡ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግሥት የገጠር ልማት ፈንድ በበጀት ድጎማ እንዲሰጥ የተወሰኑ መሆኑ እና
- በ8 ብድሮች ብር 241.9 ሚሊዮን ዕዳ ያለባቸው የአዲስ አበባ መስተዳድር እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ዕዳቸውን የመክፈል አቅም እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑ፣

ከላይ በተመለከተው ሁኔታ መክፈል የማይችሉ ድርጅቶችና የብድሮች ዝርዝር በማዘጋጀት ተጠንቶ ከመዝገብ እንዲሰረዝ በብድር አስተዳደር መምሪያ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር መቅረቡን ገልጸዋል፡፡

መሰብሰብ የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመዝገብ ስለመሰረዝ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/97 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 ላይ በተደነገገው መሠረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን እና ከሥልጣኑ በላይ የሆነውን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ በመልሶ ማበደር ሂሳብ አያያዝ የታዩትን ድክመቶች በማሰወገድ መክፈል የሚችሉትን ድርጅቶች ዕዳ በአግባቡ መከታተልና መክፈል ሲያቋርጡም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የተበደሩትን ብድር የመክፈል አቅም ያላቸውና በመክፈል ላይ ካሉ የ9 ድርጅቶች 43 ብድሮች ላይ 20 ብድሮች ኦዲት ሲደረግ ለኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ የተሰጠው 2 ብድር የሂሳብ ስራው ተጠናቆ ባለማለቁ ለኦዲት ስላልቀረበ ኦዲቱ ያልተከናወነ ሲሆን፣ በሌሎቹ 18 ብድሮች ላይ ዝርዝር ኦዲት ተደርጓል፡፡ በተደረገው ኦዲት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- <u>ወቅቱን ጠብቆ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሣብ :–</u>

  ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ በብድር ከተሰጠው ገንዘብ ውስጥ እስከ ሰኔ 30/1995 ዓ.ም ድረስ ተመላሽ መደረግ ሲገባው ያልተመለሰ ዋና ገንዘብ (Principal) ብር 171,240,441.25 እና ወለድ ብር 464,373,398.99 በድምሩ ብር 635,613,840.24 ተገኝቷል፡፡ ይኸው ሂሳብ እስከ ሰኔ 30/97 ድረስ ያልተመለሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

  ስለሁኔታው ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው ኮርፖሬሽኑ በከፍተኛ የግንባታ ሥራ ላይ በመሆኑ ክፍያውን ያዘገየው በአቅም ማነስ ችግር እንደሆነና ብድሩ የሚከፈልበትን ጊዜ ለማራዘም ወይም የእፎይታ ጊዜ ለመስጠት እየታሰበ መሆኑን፣ የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ደግሞ ኘሮጀክቱ ዘግይቶ በመጠናቀቁ ምክንያት የክፍያ ጊዜው መጓተቱንና የእዳ መክፈያ ጊዜውን ለማስተካከል ስምምነት ላይ መደረሱ ተገልጿል፡፡ ከላይ በተገለጸው መልኩ የድርጅቶቹን የእዳ መክፈያ ጊዜ ማስተካከል ከታመነበት ተገቢው እርምጃ በወቅቱ ሊወሰድ ይገባል፡፡

  በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመላሽ ያልተደረገውን ሂሳብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አበዳሪዎች ወቅቱን ጠብቆ ክፍያ የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት ለድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተመላሽ ለማስደረግ፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ድርጅቶች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ በመውሰድና ክትትል በማድረግ የመንግሥት ገንዘብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲሰበሰብ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በብድር ቁጥር IDA1704, ADB877006, ADB87022 ADB9211 እና KFW Loan ለተበደረው ሂሳብ ወለድ የታሰበው ብድሩ መከፈል እስካለበት ጊዜ (due date) ድረስ ብቻ ታስቦ ሲሆን፣ ኮርፖሬሽኑ የመክፈያ ጊዜውን አሳልፎ ክፍያ በሚፈፅምበት ወቅት እና በትክክለኛው የመክፈያ ጊዜ መካከል ባለው ጊዜ ሊከፈል የሚገባው ወለድ እንዲከፈል ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ አሰራሩ ተበዳሪ ድርጅቶች ወቅቱን ጠብቀው እንዳይከፍሉ የሚገፋፉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ወለድ መታሰብ የሚገባው ባልተከፈለው ገንዘብ ላይ ክፍያ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ያለውን ጨምሮ መሆን ስለሚገባው ለወደፊቱ ጥንቃቄ ሊደረግና ያልተሰበሰበው ወለድ ከኮርፖሬሽኑ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

- ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በብድር ስምምነት ቁጥር *3019* የተፈቀደው SDR *127,480,000* ሆኖ ሳለ እስከ *29/04/05* ድረስ SDR *134,588,741.38* ተሰጥቶ ተገኝቷል፡፡

  ተጨማሪውን SDR 7,108,741.38 በተመለከተ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና አበዳሪው ድርጅት ያደረጉት የብድር ሽግሽግ ስምምነት የቀረበ ቢሆንም፣ ተጨማሪውን ገንዘብ በተመለከተ ኮርፖሬሽኑ እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ስምምነት አላደረጉም፡፡ ስለሁኔታው ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው ስምምነት አለመፈረሙ የታወቀው ዘግይቶ መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ስምምነቱ እንዲፈረም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

  በመሆኑም ተገቢው ክትትል ተደርጎ የውል ስምምነቱ እንዲፈረም ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

**4. <u>የአገር ውስጥ ብድር ገቢ</u> :-**

መንግሥት የበጀት እጥረት ለመሸፈን አገር ውስጥ ከሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የተበደረው ሂሳብ በትክክል በገቢና በወጪ መመዝገቡን እንዲሁም በዓመታዊ ሂሣብ መግለጫ መካተቱን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 4.1 የቀጥታ ብድር ሂሣብ :–

በ1995 በጀት ዓመት የተገኘው የቀጥታ ብድር እና በበጀት ዓመቱ የተፈጸመው የዕዳ ክፍያ ትክክለኛነት ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መያዝ የነበረበት ሂሳብ ወደ 1994 በጀት ዓመት ተወስዶ በመመዝገቡ በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ሂሳብ በብር 466 ሚሊዮን አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም የ1995 በጀት ዓመት የቀጥታ ብድር ገቢ ለ1994 በጀት ዓመት የችሮታ ጊዜ ክፍያ መሸፈኛ በመዋሉና በዚሁ በጀት ዓመት በመመዝገቡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

አሠራሩ የበጀት ዓመቱን ትክክለኛ መረጃ የሚያዛባ በመሆኑ በገቢና በወጪ የሚመዘገቡ ሂሳቦች ትክክለኛውን የበጀት ዓመት ጠብቀው ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ አሰራር ከ1997 በጀት ዓመት ጀምሮ የተስተካከለ መሆኑን ኦዲት አስደራጊዎች ገልጸዋል፡፡

## 5. የውጭ አገር እርዳታ ገቢ :–

### 5.1 በትክክለኛ ዕርዳታ ሰጪ ስም ሳይመዘገብ የተገኘ ብር 127 ሚሊዮን

ከተለያዩ መንግስታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ የተገኘው እርዳታ በአግባቡ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፣ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ (ADF) የተገኘ ብር 127,038,548.97 በአፍሪካ ልማት ባንክ (ADB) እርዳታ ገቢ ውስጥ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ ይህም መረጃውን የሚያዛባና ተጠቃሚዎችን ስለሚያሳስት ሊታረምና ሲስተካከል ይገባል፡፡

### 5.2 የውጭ አገር ዕርዳታ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ለክትትል የማያመች ስለመሆኑ

በበጀት ዓመቱ መንግሥት በዕርዳታ ያገኘው ገቢ በሙሉ በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተካተተ መሆኑን ለማጣራት ተሞክሮ በቻናል 2 (Channel 2) ዕርዳታ ያገኙ ድርጅቶች ካቀረቡት ወርኃዊ ሪፖርት በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገባውን የዕርዳታ መጠን የሚገልፅ ማስረጃ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ሊቀርብ አልቻለም፡፡

በበጀት ዓመቱ ዕርዳታ አግኝተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በወርኃዊ ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶች ሂሳብ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ የሚካተትበት ሁኔታ ስለሌለ የበጀት ዓመቱ የዕርዳታ ገቢ በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሂሳብ ለመከታተል ባለበጀት መ/ቤቶች ያገኙትን ዕርዳታ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ የሚጠይቅ መሆኑን፣ የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረጉን እና ያገኙትን እርዳታ ሥራ ላይ አውለው ሪፖርት ሲያቀርቡ በተጨማሪ በጀትነት እየተመዘገበ እንደሆነ ቢታወቅም፤ ዕርዳታ አግኝተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያላደረጉ መ/ቤቶች ቢኖሩ ሊታወቅ የሚችልበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመልቲላተራል እና የመንግሥታት ትብብር መምሪያዎች ከዕርዳታ ሰጪዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ወደ አገር ውስጥ የገባውን የገንዘብ እና የዓይነት እርዳታ መጠን ለማወቅ የሚያስችል መረጃ የሚይዙ ሲሆን፣ የማዕከላዊ ሂሳብ መምሪያ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ዕርዳታ ደርሷቸው ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶችን በመከታተል ትክክለኛውን የዕርዳታ ብድር መጠን መመዝገብና በዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ ላይ ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 6. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

በዓመታዊ የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የወጪ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማጣራት በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 6.1 <u>በቀጥታ ወጪ ተይዞ ስለተገኘው ለክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የተሰጠ የድጎማ ሂሳብ ብር 4,897.4 ሚሊዮን</u>

በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የድጎማ ወጪ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ የሚገልጽ የሂሳብ ማስታወቂያ የቀረበለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ለክልሎችና ለከተማ መስተዳድሮች የተከፈለ ብር 4,897.4 ሚሊዮን ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይረጋገጥና ሪፖርት ሳይቀርብለት በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ስለጉዳዩ ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና

ደንብ መሠረት የክልል ድጎማ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበትን ሁኔታ አጠቃሎ በፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫው ውስጥ ማካተት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ኃላፊነት አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 እና አንቀጽ 74 (4) የመንግሥት ሂሳብ ሪፖርት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የተደረጉትን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች፣ የክልል መንግሥታትን የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ የበጀት ዓመቱን የመጨረሻ ሪፖርት በተጠቃለለና በተነፃፀረ መልኩ የሚይዝ እንደሚሆን እና የክልል መንግሥታትም ከፌዴራል መንግሥት የተሰጣቸውን የበጀት ድጋፍና የውስጥ ገቢያቸውን በየወሩና በየሩብ ዓመቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የድጎማ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይታወቅ የተዘጋጀው የመንግሥት ዓመታዊ የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ አቀራረብ ለፖሊሲ አውጪው አካል አሳሳችና የአገሪቱን ትክክለኛ ዓመታዊ ገቢና ወጪ አጠቃሎ የሚያሳይ በመሆኑ መታረም እንዳለበት ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ የተሰጠው ምላሽ በእኛ በኩል ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አሠራሩ የሚታረምበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡

## 7. <u>የበጀት ሂሣብ</u>

### 7.1 <u>በ1995 ዓመት የበጀት አፈጻጸምና ሥራ ላይ የዋለ በጀት ሂሣብ ኦዲት</u>

በበጀት ዓመቱ በሥራ ላይ ይውላል ተብሎ ከተገመተው ጠቅላላ የተስተካከለ በጀት ብር 19,933.7 ሚሊዮን ውስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር ባቀረበው ሂሣብ መግለጫ መሠረት በሥራ ላይ የዋለው ብር 16,382.9 ሚሊዮን ወይም የበጀቱን 82% ሲሆን፣ ለመደበኛ በጀት ወጪ የተደረገው ብር 6,903.2 ሚሊዮን በተስተካከለ በጀት ከተያዘው ብር 7,516.3 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር ብር 613.1 ወይም 8% በማነስ አሳይቷል፡፡

ለካፒታል በጀት ወጪ የተደረገው ሂሳብ ብር 4,582.3 ሚሊዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 6,324.3 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 1,742.0 ሚሊዮን ወይም 38.0% ያነሰ ሲሆን፣ ለክልሎች የተሰጠው ጠቅላላ ድጎማ ብር 4,897.4 ሚሊዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 6093.1 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 1,195.7 ሚሊዮን ወይም 24.4% አንሶ ተገኝቷል፡፡

የበጀት ዘመኑ ጠቅላላ ወጪ ብር 16,382.9 ሚሊዮን ከ1994 በጀት ዓመት ወጪ ብር 16,445.70 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር ደግሞ ብር 62.8 ሚሊዮን ያንሳል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የበጀት ዓይነት | የታወጀ በጀት | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ ወጪ | ልዩነት የተስተካከለ በጀት ከወጪ በመብለጥ/በማነስ | የ1994 በጀት ዓመት ወጪ በሚሊዮን ብር | የ1995 ከ1994 ወጪ በመብለጥ /በማነስ/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መደበኛ | 7303.9 | 7516.3 | 6903.2 | 613 | 7722.7 | (819.5) |
| 2 | ካፒታል | 3872.30 | 6324.3 | 4582.3 | 1742.0 | 4517.7 | 64.60 |
| 3 | የክልሎች ድጎማ | 6043.4 | 6093.1 | 4897.4 | 1195.7 | 4205.3 | 692.10 |
| | ጠቅላላ ድምር | 17219.6 | 19933.7 | 16382.9 | 3550.8 | 16445.7 | 62.8 |

ከላይ በሠንጠረዥ የተመለከተው ሂሣብ የበጀት አፈፃፀም በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 7.1.1 ከበጀት በላይ ሥራ ላይ ስለዋለው ብር 66.89 ሚሊዮን ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 18/1 መሠረት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዝውውር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ጥያቄ አቅርበው በማስፈቀድ በጀታቸውን አስተካክለው መጠቀም ሲገባቸው በዚሁ መሠረት ሳያስፈቅዱ የመደበኛ በጀት ብር 56.97 ሚሊዮን /ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከበጀት በላይ የተጠቀሙ መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ 1 ተመልክቷል/ የካፒታል በጀት ብር 9.92 ሚሊዮን (ከብር 100 ሺህ በላይ ከበጀት በላይ የተጠቀሙ መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ 2 ተመልክቷል) በድምሩ 66.89 ሚሊዮን ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ አድርገው ተገኝተዋል፡፡

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገው ሂሳብ አብዛኛው ከመደበኛ በጀት ሲሆን፣ ባለበጀት መ/ቤቶች ውዝፍ ሰነዶችን አወራርደው ሂሳቡን

በወጪ በመመዝገባቸው፣ የቀረጥ ክፍያ ተፈጽሞ ሂሳቡ በተጨማሪ በጀት ሳይመዘገብ ሂሳባቸውን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች በመኖራቸው እንዲሁም የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት የበጀት ዝውውር ሳያደርግ ከበጀት በላይ ተጠቅሞ በመገኘቱ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለሁኔታው ኦዲት አስደራጊዎቹ ተጠይቀው ያለፉት ዓመታት የሡነድ ሂሳቦች በጀት ሳይኖር በወጪ በመመዝገባቸው ምክንያት ሂሳቡ ከበጀት በላይ ሊታይ እንደቻለ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ መ/ቤቶቹ በሚያቀርቡት ዘገባ የገለፁ መሆኑ እና የመንግሥት ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ ከተዘጋ በኋላ የቀረጥ ሂሳብ ሪፖርት ከባለበጀት መ/ቤቶቹ በመቅረቡ ምክንያት በተጨማሪ በጀትነት ባለመመዝገቡ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በበጀት ዓዋጅ ቁጥር 282/94 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 7 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች በበጀት ዓዋጅ ያልተካተቱ ለካፒታልና ለመደበኛ በጀት ሥራ ላይ ያዋሉት የውጭ አገር ብድር የእርዳታ እና የቀረጥ ሂሳብ ሪፖርት ባደረጉት መሠረት መዝግቦ በተጨማሪ በጀትነት እንደሚይዝ የተደነገገ በአንዳንድ መ/ቤቶች ለቀረጥ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በወጪ የተመዘገበው ሂሳቡ ከመዘጋቱ በፊት በመሆኑ በጀቱንም በዚሁ ጊዜ በተጨማሪነት መመዝገብ ይቻል ስለነበር የተሰጠው ምክንያት አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የመንግሥት ሀብት በበላይነት የማስተዳደር ኃላፊነት የተጣለበት መሆኑ እየታወቀ ባለበጀት መ/ቤቶች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ተጠቅመው ሪፖርት ሲያቀርቡ ሂሳቡን እንዳለ መዝግቦ እርምጃ መውሰድ ያለበት ሌላ አካል ነው በማለት በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ጉዳይ ተከታትሎ እርምጃ ለመውሰድ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የበለጠ ሥልጣን እና ለማስፈጸም ቅርበት ያለው መ/ቤት የሌለ በመሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት እርምጃ የሚወስድበትን አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡